# የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ሱፔሪየር ፍርድ ቤት
## የወንጀል ክፍል
## ፍርድ ቤት ለመቅረብ ወይም ዋስትና ስለማስያዝና ስለመተው ማስታወቂያ

በ2ኛ፣ 5ኛ እና 6ኛ ወረዳ ውስጥ በቁጥጥር ስር መዋል፤ በነዚህ ወረዳዎች በሚገኝ የህግ አስከባሪ ድርጅት በቁጥጥር ስር መዋል

የአውራ ጣት አሻራ

**የግለሰቡ መረጃ**

| የመያዝ ቁጥር | CCN | PDID | የትውልድ ቀን |
|---|---|---|---|
| የጣቢያው ጸሀፊ/መኮንን/ባጅ/ክፍል/የCad.ቁጥር | | የጥፋት PSA | |
| የተያዘው ሰው ስም፡ **የመጨረሻ፣ የመጀመሪያ፣ መሃከለኛ** | | | |
| የሚከተለውን ጥፋት (ጥፋቶች) ስለፈጸሙ በቁጥጥር ስር ውለዋል<br>*[እባክዎ በቁጥጥር ስር ሊያስውሉ የቻሉትን ክሶች በሙሉ ይዘርዝሩ]* | | | |

## የመለቀቅና ወደ ፍርድ ቤት የመመለስ መረጃ

### ☐ በጽሁፍ ትእዛዝ ለሚለቀቁ ብቻ

*ለመኮንኖች፡፡ እባክዎ አግባብ ያለው ፍርድ ቤት ያሚገኝበትን ትክክለኛ አድራሻና የፍርድ ቤቱን ዌብሳይት በመጠቀም የመቅረቢያ ቀንን በመምረጥ ይጻፉ።*

500 Indiana Ave., NW, Washington, D.C. በሚገኘው ሱፔሪየር ኮርት ኦፍ ዘ ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ በሚባለው ፍርድ ቤት ከዚህ በታች በተጻፈው ቀንና ሰዓት ለመቅረብ ቃል ገብተው ተለቀዋል።

**ፍ/ቤት መቅረቢያ ሰዓቶች እንደክሱ (ክሶቹ)መሰረት ነው፡-**

| | |
|---|---|
| ራስን መቆጣጠር ሳይችሉ የመንዳት ጥፋቶች | **9 AM** |
| ማንኛውም ሌላ የትራፊክ ጥፋት | **10 AM** |
| ትራፊክ ነክ ሳልሆኑ ጉዳዮች ሁሉ | **11 AM** |

☐ **OAG ክስ (ክሶች) ብቻ**

______________ በ ______________
ቀን ሰዓት

**በፍርድ ቤት ቁጥር 111**

☐ **የU.S. ክስ (ክሶች) ብቻ**

______________ በ **9:30 a.m.** ፍርድ ቤት ቁጥር **C-10**
ቀን ሰዓት

☐ **U.S. እና OAG ክሶች**

______________ በ **9:00 a.m.** ፍርድ ቤት ቁጥር **111**
ቀን ሰዓት

______________ በ **9:30 a.m.** ፍርድ ቤት ቁጥር **C-10**
ቀን ሰዓት

**ይህን ፍ/ቤት ስለመቅረብ የተጻፈ ማሳሰቢያ የተቀበልኩ መሆኑን አረጋግጣለሁ። ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት ለመቅረብ ቃል እገባለሁ። ፍ/ቤት ሳልቀርብ ብቀር በዳኛ ትእዛዝ በቁጥጥር ስር ውዬ እንድቀርብ ማዘዣ እንደሚሰጥ ገብቶኛል። በተጨማሪ ፍ/ቤት ሳልቀርብ ብቀርና ባለመቅረቤ ጥፋተኛ መሆኔ በፍ/ቤቱ ከተረጋገጠ በወንጀል ጥፋተኝነት በገንዘብ ቅጣት፣ በእስራት ወይም በሁለቱም ልቀጣ እንደምችል ገብቶኛል።**

______________________ ______________
በቁጥጥር ስር የዋለው ሰው ፊርማ ቀን

### ☐ የማይመለስ ገንዘብ ማስያዝን ብቻ የሚመለከት

ክስ፡-______________________ የሚከፈል ማይመለስ ገንዘብ መጠን፡-

**$**

**ለክሱ(ለክሶቹ) የተመደበውን የማይመለስ መያዣ (ገንዘብ) መጠን ለመክፈል መርጫለሁ። ለክሱ የተመደበውን የማይመለስ ገንዘብ በመክፈሌ በፍርድ ቤት ጉዳዬ ሊሰማልኝ የሚያስችለኝን መብቴን በፈቃዴ እንድተው እንደሚያደርገኝ ገብቶኛል።**

______________________ ______________
**በቁጥጥር ስር የዋለው ሰው ፊርማ** ቀን

**<u>በቁጥጥር ስር የሚውሉ ሰዎች ሁሉ ትኩረት ሊሰጡት የሚገባ</u>**

**በድንገተኛ ሁኔታ ምክንያት ሱፔሪየር ፍርድ ቤት ዝግ ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን ከጠዋቱ 9 a.m. ፍ/ቤት መመለስ አለብዎት።**

### ☐ በፍርድ ቤት ትእዛዝ በገንዘብ ዋስትና ለሚለቀቁ ብቻ

***ለመኮንኖች: የተያዘው ሰው በዲሲ ሱፔሪየር ፍርድ ቤት ዳኛ በተሰጠ ማዘዣ የዋስትና ገንዘብ አስይዞ የሚለቀቅ ከሆነ እባክዎ ይህንን ይሙሉት***

*በወንጀል ጉዳይ ፍርድ ቤት ባለመቅረብዎ ምክንያት በዲሲ ሱፔርየር ፍርድ ቤት ዳኛ በቁጥጥር ስር ውለው እንዲቀርቡ በተሰጠ ማዘዣ በቁጥጥር ስር ውለው ነበር። ፍርድ ቤት ቁጥር* C-10, 500 Indiana Ave., NW, Washington, D.C. በሚከተለው ቀንና ሰዓት መቅረብ አለብዎት

______________ በ **9:30 a.m.**
ቀን ሰዓት

**በፍርድ ቤቱ የተወሰነውን የዋስትና ገንዘብ ከፍያለሁ። ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት ለመቅረብ ቃል እገባለሁ። ሳልቀርብ ብቀር ግን ታስሬ እንድቀርብ በዳኛ ትእዛዝ ሊሰጥ እንደሚችል ተረድቻለሁ። በተጨማሪ ፍ/ቤት ሳልቀርብ ብቀርና ባለመቅረቤ ጥፋተኛ መሆኔ በፍ/ቤቱ ከተረጋገጠ በወንጀል ጥፋተኝነት በገንዘብ ቅጣት፣ በእስራት ወይም በሁለቱም ልቀጣ እንደምችል ገብቶኛል።**

**የዋስትና ገንዘብ መጠን**

**$**

ዋስትናውን የሚያሲዘው ግለሰብ ስምና አአድራሻ

______________________
**ስም**

______________________

______________________
**አድራሻ**

______________________ ______________
***የታሳሪው ግለሰብ ፊርማ*** ***ቀን***

### ☐ ጁሪዎች ብቻ

በዲሲ ሱፔሪየር ፍርድ ቤት በጁሪነት እንዲያገለግሉ ተጠርተው ባለመቅረብዎ ከፍርድ ቤት በተሰጠ የይታሰሩ ትእዛዝ በቁጥጥር ስር ውለዋል። በዛሬው እለት በዲሲ ሱፔሪየር ፍርድ ቤት የክፍል **ቁጥር 3130** በአድራሻ [The Jurors' Office], 500 Indiana Ave., NW, Washington, D.C. ከዚህ በታች በተጻፈው ቀንና ሰዓት ቀርበው ሪፖርት እንዲያደርጉ ይለቀቃሉ፡-

በሚቀጥለው የስራ ቀን በ **9:30 a.m.**
ቀን ሰዓት

**ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት ለመቅረብ ቃል እገባለሁ። ፍ/ቤት ሳልቀርብ ብቀር በዳኛ ትእዛዝ በቁጥጥር ስር ውዬ እንድቀርብ ማዘዣ ሊሰጥ እንደሚችል ገብቶኛል። በተጨማሪ ፍ/ቤት ሳልቀርብ ብቀርና ባመቅረቤ በፍ/ቤት ጥፋተኝነቴ ከተረጋገጠ በገንዘብ ቅጣት፣ በእስራት ወይም በሁለቱም በወንጀል ጥፋተኝነት ልቀጣ እንደምችል ገብቶኛል።**

______________________ ______________
***የታሰረው ግለሰብ ፊርማ*** ***ቀን***

### ☐ በቁጥጥር ስር ለዋሉ የሚሰጠውን መግለጫ ስለመቀበል ማረጋገጫ

**በቁጥጥር ስር ለዋሉ ሰዎች የሚሰጠውን መግለጫ የተቀበልኩና ያነበብኩ መሆኔን እንዲሁም ያሉኝ መብቶች ምን እንደሆኑ የገባኝ መሆኑን አረጋግጣለሁ።**

______________________ ______________
የታሰረው ግለሰብ ፊርማ ***ቀን***

አድራሻ:______________________

የስልክ ቁጥር:______________________ ኢሜይል:______________________

በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ፍ/ቤት ተጠባባቂ ጸሀፊ ተሰጠ

______________ ______________ ______________
የጣቢያው ጸሀፊ ፊርማ የባጅ ቁጥር ክፍል

# በቁጥጥር ስር ለዋሉ ሰዎች ማስታወቂያ

*እባክዎ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የመለቀቅዎን ሁኔታና ማድረግ የሚገባዎትን የሚያብራሩ መረጃዎች ይገምግሙ። ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መረጃዎች ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ ሊቀየሩ ይችላሉ።*

## ☐ በጽሁፍ ትእዛዝ መለቀቅ

በዚህ ሰነድ ገጽ 1 ላይ በጽሁፍ ትእዛዝ መለቀቅ የሚለው ክፍል ላይ በጽሁፍ ትእዛዝ ለመለቀቅ ብቁ ሆነው ከተገኙ 500 Indiana Ave., NW, Washington, D.C. ከሚገኘው ዲሲ ሱፔሪየር ፍርድ ቤት በጽሁፍ ትእዛዙ ላይ በተጠቀሰው **ቀንና ሰዓት** ለመቅረብ ቃል ገብተው ወዲያውኑ ሊለቀቁ ይችላሉ።

አቃቤ ህግ እርስዎን በወንጀል ለመክሰስ ወይም ላለመክሰስ ውሳኔ ይሰጣል። ፍ/ቤት ካልቀረቡ የፍ/ቤቱ ዳኛ እርስዎን በቁጥጥር ስር ውለው እንዲቀርቡ ትእዛዝ ሊሰጡ ይችላሉ። በተጨማሪ አቃቤ ህግ ክስዎን ውድቅ ለማድረግ ቢወስንም እንኳ ሳይቀርቡ በመቅረትዎ ተጨማሪ ክስ ሊመሰረትብዎ ይችላል።

ፍርድ ቤት እስከሚቀርቡበት ግዜ ድረስ በጽሁፍ ትእዛዝ መለቀቅዎ በገደብ ሆኖ ይህም ገደብ የተወሰነ ሰው ወይም ሰዎች እንዳይቀርቡና ምንም ግንኙነት እንዳያደርጉ እና/ወይም የተወሰነ ቦታ እንዳይሄዱ ሊሆን ይችላል።

እንዳትደርሱ ተብለው የተሰጠዎትን ትእዛዝ ከጣሱ የፖሊስ መኮንን ወዲያውኑ በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ሊያደርግዎትና ከተያዙበት ቀን ቀጥሎ ባለው የስራ ቀን ወደ ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ ይደረጋል። አቃቤ ህጉ በሆነ ወንጀል ክስ ሊመሰርትብዎ ቢወስን እንኳ በጠበቃ የመወከል መብትዎ የተጠበቀ ይሆናል። ጠበቃ ለመቅጠር አቅምዎ የማይፈቅድ ከሆነ ጠበቃ ይመደብልዎታል።

### ጠቃሚ መረጃ

ምንም እንኳ በቁጥጥር ስር ውለው የነበሩ ቢሆንም መንግስት በእርስዎ ላይ ፍርድ ቤት ክስ ላለመመስረት ውሳኔ ላይ ሊደርስ ይችላል። ለመጀመሪያ ቀን ፍርድ ቤት በሚቀርቡበት ቀን የተለቀቁበትን የጽሁፍ ትእዛዝ ፎርም ይዘው ፍርድ ቤት መምጣት አስፈላጊ ነው ምክንያቱም መንግስት በእርሶ ላይ ክስ መመስረትና አለመመስረቱን ለማወቅ የሚያስፈልግዎ መረጃ በፎርሙ ላይ ስላለ ነው።

### ለጉዳይ መረጃ

ጉዳይዎ ያለበትን ሁኔታ መረጃ ለማግኘት የD.C. Superior Court Criminal Division የሚደውሉበት የደግበኞች አገልግሎት መስመር የስልክ ቁጥር **(202) 879-1373** ነው።

## ☐ በገንዘብ ዋስትና ለሚለቀቁ

በዳኛ ትእዛዝ በቁጥጥር ስር ውለዋል። ትእዛዙን የሰጡት ዳኛ በወሰኑት መሰረት የዋስትናውን የገንዘብ መጠን አሲዘው ሊለቀቁ ይችላሉ። በዚህ ሰነድ በገጽ 1 ላይ እንደተጠቀሰው የዋስትናውን ገንዘብ ካስያዙ ፍርድ ቤት በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት እንዲቀርቡ ሆኖ ይለቀቃሉ። በተባለው ቀንና ሰዓት ካልቀረቡ በቁጥጥር ስር ውለው እንዲቀርቡ አዲስ የዳኛ ትእዛዝ ሊተላለፍብዎ ይችላል። ምናልባት አቃቤ ህግ ክስዎን ውድቅ ለማድረግ ቢወስንም እንኳ ሳይቀርቡ በመቅረትዎ ተጨማሪ ክስ ሊመሰረትብዎ ይችላል።
በተጨማሪ በቀጠሮው ቀን ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ መቅረትዎ በዋስትና ያስያዙትን ገንዘብ እንዲያጡ ሊያደርግዎ ይችላል።

## ☐ የማይመለስ ገንዘብ ከፍለው መለቀቅ

የተከሰሱበት ጥፋት የማይመለስ ገንዘብ ከፍለው እንዲለቀቁ ለማድረግ ብቁ ሊሆኑ የሚያስችልዎ ከሆነ በፍርድ ቤቱ የተወሰነውን የማይመለስ ገንዘብ ከፍለው ጉዳዩ በዚሁ እልባት እንዲያገኝ ሊያደርጉ ይችላሉ። የተወሰነውን የገንዘብ መጠን ለመክፈል ከመረጡ ገንዘብዎ **አይመለስልዎትም** ምክንያቱም ገንዘቡን መክፈልዎ እንደማይመለስ መስማማትዎ ነው። የማይመለሰውን ገንዘብ ከከፈሉ ምንም እገዳ፣ ቅጣት፣ የተሻሻለ ፍርድ ወይም የፍታብሄር አለማስቻል በማንኛውም የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ፍርድ ቤት ወይም ድርጅት በማንኛውም ቀጣይ የወንጀል፣ የፍታብሄር ወይም አስተዳደራዊ ስርዓት ወይም እርምጃ አይወሰድብዎትም። መታሰርዎ **ተመዝግቦ** ይቀመጣል። የእስር መዝገብዎ የተዘጋ እንዲሆን ለሱፔሪየር ፍርድ ቤቱ ማመልከት ይችላሉ። የእስር መዝገብዎን ስለማዘጋት ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ Public Defender Service በስልክ ቁጥር **202-628-1200** በመደወል ወይም በኢሜይል **www.pds.dc.org** ይጠይቁ።

- ***ሀሳብዎን ከቀየሩና ክሶቹን ለመቃወም ከፈለጉ ምን ሊሆን ይችላል?*** ገንዘቡን ካስያዙ በሁዋላ ምናልባት ፍርድ ቤት መቅረብ ይሻለኛል ብለው ቢወስኑ “Motion to Set Aside Forfeiture” በመባል የሚታወቀውን አቤቱታ ከዛሬ ቀን ጀምሮ በ90 ቀናት ውስጥ ማቅረብ አለብዎት።

- ***ምናልባት መንግስት የእርስዎን የማይመለስ ገንዘብ የመክፈልዎን ውሳኔ ቢቃወምስ?*** በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ አቃቤ ህግ ጽ/ቤት ለዚህ ጉዳይ የተመደበው አቃቤ ህግ “Motion to Set Aside Forfeiture” በመባል የሚታወቀውን አቤቱታ በ90 ቀናት ውስጥ ማቅረብ አለበት።

- ***ምናልባት ፍ/ቤቱ የቀረበለትን አቤቱታ ካጸደቀ ምን ሊሆን ይችላል?*** ምናልባት የእርስዎ ወይም የመንግስት አቤቱታ ተቀባይነት ካገኘ ክሱ እንደገና እንዳለ ይሆንና እርስዎ ፍርድ ቤት በመቅረብ ጉዳዩ ይቀጥላል። ጠበቃ ለመቅጠር አቅም የማይኖርዎ ከሆነ በፍርድ ቤቱ የተሰየመ ጠበቃ ለማግኘት ይችሉ ይሆናል። ምናልባት የማይመለስ ገንዘብ ለመክፈል ካልፈለጉና የወንጀሉን ጉዳይ ለመቀጠል ከመረጡ በጽሁፍ ትእዛዝ ለመለቀቅ ብቁ ነዎት።

## ☐ በትራፊክ ጥፋቶች ምክንያት ለታሰሩ የሚሆን ጠቃሚ ማሳሰቢያ

ምናልባት ***መንጃ ፈቃድ ባለመኖር፣ እንዳይነዱ ከታገዱ በኋላ*** ወይም ***ፍቃድዎ እንዲመክን*** ከተደረገ በኋላ ተይዘው ታስረው ከነበረ በቀጠሮዎ ቀን የሚከተሉትን ሰነዶች ይዘው ቢቀርቡ ጉዳይዎ ቀደም ብሎ እልባት እንዲያገኝ ለማድረግ ይጠቅም ይሆናል፡-

- ***መንጃ ፈቃድ አለመኖር፡-*** ያልተቃጠለ መንጃ ፈቃድ (ወይም ከDistrict of Columbia Department of Motor Vehicles (DMV) የተሰጠ ያልተቃጠለ የተለማማጆች ፈቃድ ወይም ያልተቃጠለ የሌላ ክፍለ ግዛት ፈቃድ **እና** የ15 ዓመት የመንጃ ታሪክ)
- ***ከታገዱ ወይም ፍቃድዎ እንዲመክን ከተደረገ በኋላ ሲነዱ ከተገኙ፡-*** ምናልባት ፈቃድዎ ከታገደ ወይም እንዲመክን ተደርጎ ከሆነ ከDistrict of Columbia Department of Motor Vehicles ወይም ከሚኖሩበት ክፍለ ግዛት Department of Motor Vehicles መ/ቤት ፈቃድዎ እንዲታገድ ወይም እንዲመክን የሆነበትን ምክንያት እንዲታረም ያደረጉ መሆንዎን የሚያሳይ ሰርቲፋይድ የሆነ ሰነድ ያቅርቡ ከዚሁም ጋር ያለብዎትን ትኬቶች መክፈልዎን ወይም የልጅ ማሳደጊያ ግዴታዎን የተወጡ መሆንዎንና ፈቃድዎ እንደገና እንዲሰራ መክፈል ያለብዎት ክፍያ ካለ መክፈልዎን የሚያሳይ መረጃ ማቅረብ አለብዎት። የሚያቅርቡት ሰነድ ፈቃድዎ እንደገና እንዲሰራ የተደረገ መሆኑንና ምንም ችግር የሌለብዎት መሆኑን ማሳየት አለበት።